መጽሐፍ የኣሲምባ ፍቅር

ደራሲ ካህሳይ አብርሃ (አማኑኤል)

ጠያቂ ኃይሉ በለሳ

# ጥያቄዎች

ሰላም ጉዋድ አማኑኤል፤

በመጀመሪያ አንተም እንዳልከው ሽፈራውም ደግሞታል የአሲምባ ፍቅር ለሰዎች ወደኍዋላ ተመልሰው በታሪካቸው ዙሪያ እንዲወያዩ ዕድል ስለሰጣቸው ከልብ ለትደሰት ይገባሃል። ጉዋድ ሽፈራው የሰጠውን ትችትና አንተም የሰጠኸውን መልስ ተመልክቸ ሁላችንም በቁም ነገሩ ላይ ብቻ መነጋገር የበለጠ ውጤታማ ያደርገናል ብየ ስለአመንኩ ጥቂት ጥያቄዎች ለመጠየቅ ወሰንኩ። እኔ ዘሬ አማራ ነኝ። ሁሉንም አማራ በጅምላ አልወድም እንዲሁም ደግሞ ሌላ ዘር ያላቸውን ሌላ ሃይማኖት የሚከተሉትን በአጠቃላይ ከእኔ በመለየታቸው በጅምላ አልጠላም። በልጅነት እድሜየ በትምህርት ቤት ወይም በሰፈር እሴትም ሆኑ ወንዶች አማራ ያልሆኑ ጉዋደኞች ነበሩኝ ከነዚህ ልጆች ጋር ስንጣላም ይሁን ስንፋቀር አንተ እንትን አንቺ እንትን እንባባል ነበር እንጅ ከዚያ ያለፈ የሚውል የሚያድር ቂምና ጥላቻ ወይም መናናቅ ኑሮን አያውቅም። ከአደኩ በኍዋላ በረሃም እያለን ይሁን በስደት በአመለካከትና በባህሪ እንጅ በዘር ወዳጅነት ፈጥሬ አላውቅምና ከዘር እንጻር ያልኩት ወይም የምለው ነገር እንደሌለኝ ላረጋግጥልህ እወዳለሁ።እንዲያውም በረሃ እያለንማ አይደለም የትግራይ ተወላጆች ቀርቶ ኤርትራውያን ሳይቀሩ ከፊቴ ላይ በቆራጥነት ለኢትዮጵያ አንድነት ለህዝብ እኩልነትና ነፃነት ሲወድቁ ያይን ምስክር ነኝና ኢህአፓ/ኢህአሠ ወስጥ ለነበሩ ታጋዮች የዘረኝነት ቅፅል አይሰጣቸውም ባይ ነኝ። አሁን ያላቸውን አመላከከት መተቸት ይቻላል።ይህን ካልኩ በኍዋላ በጣም የማደንቀው አንድ ሰው በዘር እየተጠላና እየተበደለ ያ ነገር በእሱ አዕምሮ ውስጥ ስሌለ ከግምት ውስጥ ባለማስገባት ዘረኞቹን ተቀናቃኞቹን አሳፍሮ የሚኖር እኔም አንተም የምናውቀውን ፕሬዚደንት ኦባማን ልጠቅስልህ አወዳለሁ። ለማንኛውም ሁላችንም ፅንፈኝነትን ወደ ኍዋላ ትተን ረጋ ባለ መንፈስ በቁምነገሩ ላይ እንነጋገር።

አሁን ወደ ጥያቄዎቸ ለመልስህና

1. አንተ ወደ ኢህአፓ/ኢህአሠ ስትገባ በፈቃድህ ሄድክ ድርጅቱ ባይቀበልህ ኑሮ ለኢትዮጵያ ጭቁን ህዝብ ያበረከትከውን ተጋድሎ ባላደረክም ነበር።በምትለቅበትም

ጊዜ ወደህ ስትመጣ ፈቅዶ የተቀበለህን ድርጅት ነግረህ ስላልሄድክ የሚባለው ከድተህ ሄድክ ነው። ለመሆኑ በመክዳትና በማፈግፈግ መካከል ልዩነት ይኖር ይሆን?

2. ለሽፈራው ትችት መልስ ስትሰጥ የወሎን የአርባያን የእብናትን የውቅሮን የነበለትን ወዘተ ጦርነቶች አንዳቸውም ትክክል እንዳልሆኑ ዘርዝረሃል ለስህተቱ ተጠያቂውም የድርጅቱ ከፍተኛ አመራር እንደሆነ ነው። ይህን ስል ድርጅቱ ስህተት አልሰራም ለማለት አይደለም የተሰራውም ስህተት ነው ለዚህ ያበቃን። ለመሆኑ ኢህአፓ/ኢህአሠ የሰራው ትክክለኛ ነገር ነበር ትላለህ ወይ? ኖረም አልኖረም ከላይ የተዘረዘሩትን ልዩነቶች አቅርቦ ከድርጅቱ መለየት እንደሚቻል ታውቅ ነበር ወይ?
3. ከጕዋዲት ድላይ ጋር በፍቅር ተመስጣችሁ መሳሪያ ተባርቆ ድምፁን ሰምተህ ከወታደራዊ ጥንቃቄ አንጻር ሁኔታውን ለማጣራት ወደውጭ ወጣህ ከእናንተ በሰከነ መንገድ ሁኔታውን የመልከተችው አርሶ አርሶ አደር ተኩሱ ከእናንተ የወጣ እንጅ ከውጭ አለመሆኑን ስትነግርህ ተመለስክ  በተለይ መሳሪያው በጕልበቷ መካከል ከሆነ የመንፈራገጥ ወይም ለመንጠቅ የመሞከር ባህሪ አልነበረውም ወይ? ሶስት ጥይት ሲተኮስ ጭስ አልነበረውም? የባሩዱ ሽታስ የት ሄደ? በጣም የገረመኝ ደግሞ ሶስቱ ቀለሆች ከጥይቱ ጋር ሄዱ ወይስ ከእናንተ ፊት እንዴት ዱብ ዱብ አላሉም?
4. የድላይና የአንተን የፍቅር ግንኙነት አንዳላዩ እያዩ ያለፉት ጥቂት ጕዋዶች እንደነበሩና ባለማጋልጣቸው ያመሰግንካቸውና ቢያጋልጡን  ሁለታችንም ምን አይነት ቅጣት ይደርስብን ነበር ትላለህ በሌላ በኩል ፈተናውን ተወጣን እንጅ ምንም ወንጀል አልሰራነም ትላለህ ይህ እራሱን በራሱ አይቃረንም ወይ?
5. እኔ እስከማውቀው ድረስ ማለት ኢህአፓ ለአባላቱ  በፅሁፍም ይሁን በማዋቅር ያስተላልፍ የነበረው መልክት ከትግራይ ነፃ አውጭ ግንባር ጋር ወደ ዘጠኝ ጊዜ ያህል ለውይይት ተቀምጠው እንድነበርና በዘጠኙም ስብሰባዎች ወያኔዎች ስብሰባውን ረግጠው እንደወጡ ወይም ለመልካም ግንኙነት የታሰበውን እንደሚያበላሹት ነበር የተነገረን ከአሲምባ ፍቅር ላይ እንደትረዳሁት ከዚህ በተቃራኒው ይመስላልና ሁኔታውን ብታአብራራልኝ?
6. አማኑኤል በአሲምባ ፍቅር መግብያህ አንዳንድ የረዱህ ሰዎችን ስም ጠቅሰህ አመስግነሃል በመፃህፉ ውስጥ ግን ሁሉንም አንተ እንደምታውቀው እንጅ እገሌ እንዳለው ወይም እግሊት እንዳለችው የተባለ ወይም በትምህርተ ጥቅስ ውጥ የተቀመጠ ነገር አላየሁምና ይኸንስ እንዴት ታየዋለህ?

ማሳሰቢያ

አማኑኤል ከቻልክ ለጥያቄዎቹ በቅደም ተከተላቸው  ረጋ  ባለ መንፈስ መልስ ስጥ ካልቻልክ እንደተለመደው ዝምታ ይሻላል እንጅ ወደ ዘር ባትመልሠው ለአንተ ጥሩ ይሆናል እላለሁ። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ኢያቱ ባይሆን ቅድመ አያቱ በዘር

ያልተደባለቀ የለም አለመታደል ሆነና  በንጉሡ ጠቅላይ ግዛት በደርግ ክፍለ ሃገር በኢህአደግ ዘርን መሰረት ያደረገ ክልል የሚል የከፋፍለህ ግዛው ቅኝት ተሰንቅሮ በእኛ ዘመን የዘር ልዩነት ጠንክሮና መልኩን ቀይሮ በመስተናገዱ ለዚህ ጉድ ተጋልጠናል እንጅ እነዚህ ዘሮች ቅድመ ዓለም ጀምረው አብረው ኑረዋል። ቀዝቀዝ እንበል።
አመሰግናለሁ
ኃይሉ በለሳ